አሐዱ፡ባንክ
Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com


አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

ይቻላል
It's Possible!


ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com



# ንግድና ልማት

ህዳር 2016 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com


## የአዲስ አዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ታህሳስ 11 2016 አ.ም 17ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ለማካሄድ ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ አስታወቀ

**በስታፍ ሪፖርተር**

ከሰባት አስርት አመታት በላይ ያስቆረውና በሺዎች የሚቆጠሩ የንግድ ተቋማትን በአባልነት ያቀፈው የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት( አዲስ ቻምበር) በኢትዮጵያ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ትልቁን ድርሻ ይይዛል::



ከጊዜ ወደ ጊዜ የአባላቱ ቁጥር ከፍ እያለ የመጣው ይህ ምክር ቤት በየሁለት አመት የቦርድ ምርጫ በማካሄድ ፕረዚደንትና የቦርድ አባላትን የሚመርጥ ሲሆን በየአመቱ ደግሞ ጠቅላላ ጉባኤውን ያካሂዳል:: በመሆኑም ምክር ቤቱ በመጪው ታህሳስ 11 ቀን 2016 ዓ/ም በኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል 17ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን እንደሚያካሄድ አስታውቋል::

ጠቅላላ ጉባኤው የ2015 በጀት ዓመት የሥራ ክንውንን እንደሚገመግምና የውጭ ኦዲተሮች የሚያቀርቡትን ሪፖርት መርምሮ እንደሚያጸድቅ ይጠበቃል:: ምክር ቤቱም አባላቱ በዚህ ጉባኤ ላይ በንቃት በመሳተፍ የአባልነት ግዴታቸውን እንዲወጡ ጥሪውን አቅርቧል::

## 14ተኛው የአዲስ ቻምበር አለም አቀፍ የእርሻ እና ምግብ ንግድ ትርኢት የኢትዮጵያን የግብርና ሀብት በስፋት ያስተዋወቀ እንደነበር ተገለጸ

**በስታፍ ሪፖርተር**

የአዲስ አበባ ንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በየአመቱ ከሚያካሂዳቸው ዋና ዋና ንግድ ትርኢቶች መካከል አንዱ የሆነው አዲስ ቻምበር አለም አቀፍ የእርሻ እና ምግብ ንግድ ትርኢት ለ14ተኛ ግዜ በአዲስ አበባ ሚሌንየም አዳራሽ በተሳካ መልኩ ተካሂዷል::

ከህዳር 27 እስከ ህዳር 29 2016 አ.ም የቆየው 14ኛው አለምአቀፍ የእርሻና የምግብ ንግድ ትርኢት በደማቅ ሁኔታ የተከፈተ ሲሆን በዚህ የንግድ ትርኢት ላይ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች ተሳታፊ ሆነዋል::

በመክፈቻ ስነስርአቱ ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ምክትል ቢሮ ሃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ



አምባሳደሮች፤የምክር ቤቱ ቦርድ አባላት ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እና የንግድ ትርኢቱ ተሳታፊዎች ታድመዋል::

በወቅቱ ንግድ ትርኢቱን በይፋ ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ምክትል ቢሮ ሃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ ባደረጉት ንግግር የግብርናው ዘርፍ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚገኘው የኢኮኖሚ ብሎም የማህበራዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ በልማት እቅዱ ውስጥ በልዩ ትኩረት መካተቱ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል::

አክለውም የከተማ አስተዳደሩ ንግድ ምክር ቤቱ እያከናወነ ያለውን የሃገር ውስጥ እና የውጭ ኩባንያዎችን ለቴክኖሎጂ ሽግግር ብሎም ከተማዋን ምቹ የኢንቨስትመንት መዳረሻ መሆኗን ለማሳውቅ የሚያደርገውን ጥረት እውቅና እንደሚሰጡት ገልጸዋል::

የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው ንግድ ትርኢቱ በምክር ቤቱ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን በንግግራቸው አንስተው የሃገራችንን የወጭ ንግድ አስመልክቶ የፖሊሲ፤የሎጅስቲክ እና የትራንስፖርት እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና ሌሎችም

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirmamecha@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
ከፍያለው ዋሲሁን
ካሳሁን ማሞ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ህዳር 2016 እትም

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# ርዕሰ አንቀጽ

## ኀላፊነት የሚሰማው የቢዝነስ ስነምግባር ለተሻለ ምርታማነትና ስራ ፈጠራ!

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከተቋቋመባቸው አላማዎች አንዱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ፤ አመቺ ንግድ ነክ ፖሊሲዎች እንዲወጡና ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም ዘላቂ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ተግባራዊ እንዲደረግ የፖለሲ አድቮኬሲ ስራን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የቢዝነስ አውድ በፈጣን ሁኔታ ተለዋዋጭ በሆነበት በዚህ ወቅት ደግሞ ንግድ ምክር ቤቱ የንግድ ክንውኖች ዘላቂ እና ኀላፊነት በተሞላበት ሁኔታ እንዲተገበሩ የንግዱ ህብረተሰብ ግንዛቤ እንዲያድግ ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው የቢዝነስ ስነ ምግባር (RBC) ዓለም አቀፍ የንግድ ጽንሰ-ሐሳብ እንደመሆኑ መጠን የንግዱ ማህበረሰብ ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በማስወገድ፣ በማስተካከል እና በመቅረፍ ለዘላቂ ልማት አዎንታዊ አስተዋጽዖ በማድረግ የንግድ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ምክር ቤቱ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

የንግዱ ማህበረሰብ በአለም አቀፍ ደረጃ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆን ኀላፊነት የሚሰማው የንግድ ስነ ምግባር መተግበር ለነገ የሚተው ጉዳይ አለመሆኑን በጽኑ ያምናል፡፡ እንደ ግብርና የመሳሰሉ ምርቶች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አለምአቀፋዊ በሆኑበት በዚህ ወቅት ከአምራቾች ወደ ቸርቻሪዎች ብሎም ወደ ሸማቾች በሚደርሱበት ወቅት ኀላፊነት በተሞላበት መልኩ መመረት እንዳለባቸውና ይህን ተግባራዊ ማድረግ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እውን እንዲሆን ፤ የተሻሻለ የአቅርቦት ሰንሰለት እንዲፈጠር፤ የዜጎች የኑሮ ሁኔታ፤ ጤናና ደህንነት ይበልጥ እንዲሻሻል የሚያበረክተውን አስተዋጾ ይረዳል፡፡

ከዚህም ባለፈ ንግድ ምክር ቤቱ የቢዝነስ ተቋማት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ሂደት በሰብአዊ መብቶች ላይ፤ በህብረተሰቡ እና በአካባቢ ላይ ጎጂ እና አሉታዊ ተጽዕኖን ሊከላከል የሚችል አወቃቀሮችን እና አሠራሮችን በመዘርጋት ስራቸውን እንዲያከናውኑ የጀመረውን ድጋፍ አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

# 14ተኛው የአዲስ ቻምበር አለም አቀፍ...

ከ ገጽ 1 የዞረ





ችግሮች ያሉበት መሆናቸውን አንስተው እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በመንግስት የሚደረጉ ተስፋ ሰጭ ጥረቶች መኖራቸውን አንስተዋል::

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማሪያም በንግድ ትርኢቱ መክፈቻ ንግግራቸው የንግዱን ዘርፍ በማጠናከር በሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጉልህ ድርሻ እያበረከተ እንደሆነ ተናግረዋል::


የተለያዩ የአምራችና የቴክኖሎጅ ኩባንያዎች ዘመኑ የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠቀም ያመረቷቸውን ምርቶችና የሚሰጡትን አገልግሎት ለማስተዋወቅና ተደራሽነታቸውን ለማስፋት የርስ በርስ ልምድ የሚለዋወጡበት መድረክ መሆኑን ዋና ጸሀፊው ተናግረዋል::

ለሶስት ተከታታይ ቀናት በዘለቀው ንግድ ትርኢት ላይ በግብርና ምርት እንዲሁም በማቀነባበር ዘርፍ የተሰማሩ የሃገር ውስጥ እና የውጭ ኩባንያዎች የንግድ ትስስርና የገበያ እድል እና ምርታቸውን ያስተዋወቁበት መድረክ እንደነበር ተሳታፊዎች ገልጸዋል::

ከህዳር 27 እስከ ህዳር 29 2016 ኢ.ም የቆየው 14ኛው አለምአቀፍ የእርሻና የምግብ ንግድ ትርኢት በርካታ ዝግጅቶች የቀረቡበት ሲሆን ከነዚህም መካከል አውደጥናት ይገኝበታል:: በዚህ የእርሻና የምግብ አውደርእይ ላይ ሲምፖዚየም የተካሄደ ሲሆን በተለይም የአፈሪቃ ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት ለኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች አስተማማኝ ገበያን በመፍጠር የሚኖረው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን በነበረው የውይይት መድረክ ላይ ተገልጿል:: ይህን የገበያ እድል ለመጠቀም በግብርና ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች በተለይም ምርቶቻቸው ላይ እሴት በመጨመር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ጥሪ ቀርቧል::

ለሶስት ቀናት የቆየው 14ኛው አለምአቀፍ የእርሻና የምግብ ንግድ ትርኢት በስተመጨረሻም የተለያዩ የመዝጊያ ፕሮራሞችን በማካተት ህዳር 29 ቀን የተጠናቀቀ ሲሆን ለዝግጅቱ መሳካት አስተዋጾ ያደረጉ የንግድ ተቋማትና በእለቱ ምርጥ የኢግዚቢሽን መድረክ በማዘጋጀት የተመረጡ ኩባንያዎች ተሸላሚ ሆነዋል::

# የሽያጭ ሰራተኞች ዘመኑን የዋጀ ስራ ለመስራት በእውቀት ላይ የተመሰረተ አሰራርን ሊከተሉ እንደሚገባ ተገለፀ




አዲስ ቻምበር የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ተደራሽነት ለማስፋት የሽያጭ ሰራተኞችን አቅም በማሳደግ ውጤታማ ስራን ለመስራት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል:: የዚህ አንድ አካል የሆነው ለሽያጭ ሰራተኞች የተዘጋጀው የሽያጭና ገበያ አፈላለግ ላይ ትኩረቱን ያደረገው ስልጠና በቅርቡ ተካሂዷል::

የገበያ ወይንም ማርኬቲንግ ስራ እየተራቀቀ ሄዷል ፤ የሽያጭ ሰራተኞችም ከጊዜው ጋር አብሮ የሚሄድ አሰራር እንዲከተሉ በማሰብ የተዘጋጀ ስልጠና መሆኑ በወቅቱ ተገልጿል ::

የምክር ቤቱ የኮሚኒኬሽንና አባላት ጉዳዮች ምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ስዩም ጫኔ የሽያጭ ሰራተኞች ለምክር ቤቱ ያደረጉትን አስተዋፆ በማድነቅ ዘመኑ የሚፈለገውን አሰራር ማወቅና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ስራ በመስራት ምክር ቤቱን አገልግሎት ይበልጥ ማስተዋወቅ ይጠበቅባችኃል በማለት ጥሪ አስተላልፈዋል::

ንግድ ምክር ቤቱን በኢትዮጵያ ንግድ እንዲስፋፋ ንግድ ስራ እንዲሳለጥና የንግድ ስራ እንዲስፋፋ እየሰራ እንደሚገኝ አስታወሰዋል:: ምክር ቤቱ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ምንነትና ፋይዳ በተመለከተ ለሽያጭ ሰራተኞች ያብራሩት አቶ ስዩም ምክር ቤቱ እንደ ዳሬክተሮች ተቋም ኢንስቲትዩት መሰል አዳዲስ ተቋማትን አላማ በተመለከተ ገለፃ አድርገዋል ::

የምክር ቤቱ ለውጦችን እና የአባላትን ፍላጎት አውቃችሁ ወደ ንግዱ ማህበረሰብ በመቅረብ አዲስ ቻምበር ምን ይሰራል ፤ ምን እንጠቃማለን የሚለውን ለማስተዋወቅ ይረዳችኃል ብለዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ ከ200ሺ በላይ ነጋዴዎች ይገኛሉ ተብሎ እንደሚታመን የጠቀሱት አቶ ስዩም ፤ የንግዱን ማህበረሰብ ምርቶችና አገልግሎቶች በስፋትና በጥራት ለማስተዋወቅ ሰፊ እድል እንዳለ ጠቁመዋል::
በመሆኑም ንግድ ምክር ቤቱ በከተማዋ የሚገኙ ነጋዴዎች አባል የማድረግ ስራ ከሽያጭ ሰራተኞች እንደሚጠበቅ ተናግረዋል::

የአዲስ ቻምበር አባላት ምክር ቤቱ የእኔነት ባለቤትነት እንዲስማቸው የሽያጭ ሰራተኞች ሚና የላቀ መሆኑን ጠቅሰዋል :: በስልጠናው ላይ የተሳተፉ የሽያጭ ሰራተኞች በበኩላቸው ምክር ቤቱ ለሽያጭ ሰራተኞች ስልጠና በማዘጋጀት ውጤታማ ስራ እንዲሰሩ የማድረግ ጅማሮውን አድንቀዋል::

ሰልጠናው በቀጣይ ስራቸው ላይ አዎንታዊ አስተዋፆ እንደሚኖረው ገልፀው ፤ መሰል ስልጠናዎችም በቀጣይነት እንዲዘጋጅ ጠይቀዋል :: ሰልጠናው የአንድ ጊዜ ብቻ እንደማይሆን የተናገሩት አቶ ስዩም አዳዲስ አባላትን ማፍራት ላይ ፤ ነባር የምክር ቤቱን አባላትን ጠብቆ በማቆየት እና የምክር ቤቱን ምስል ይበልጥ ማጉላት የሚያስችሉ ስራዎችን እንዲሰሩ የሚያስችሉ ስራዎችን ምክር ቤታቸው እንደሚሰራ አረጋግጠዋል ::

# የሎሚና ነጭ ሽንኩርት ምርትና ምርታማነትን በስፋትና በጥራት ለማምረት እንዲቻል መንግስት ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ጥናቶች ጠቆሙ



**በከፍያለው ዋሲሁን**

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በሎሚና ነጭ ሽንኩርት የእሴት ሰንሰለት ላይ ጥናት በማስጠናት የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት እንዲወያዩ አድርጓል። የሎሚ ምርት እንደ ቡና ፣ ሙዝ ፣ አቡካዶ ፣ ሁሉ ወደ ውጭ ገቢያ በመላክ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት የሚያስችል አቅም እንዳለው አቶ አማረ አዱኛ ባቀረቡት ጥናት አመልክተዋል።

ከሆርቲካልቸር ምርቶች መካከል ለአበባ ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱን የጠቀሱት አቶ አማረ ፤ ይሁንና ሎሚ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት የሚያስችል እምቅ አቅም ቢኖረው ትኩረት ተነፍጎታል ብለዋል ።

አሁን ላይ ሎሚ በአርሶ አደር ደረጃ እየተመረተ ይገኛል ያሉት ጥናት አቅራቢው ፤ የተሻሻለ ምርጥ ዘር አለመኖር ፣ በሰፋፊ እርሻዎች ባለመመረቱ ከዘርፉ መገኘት ያለበትን የውጭ ምንዛሬ እያስገኘ አለመሆኑን ገልፀዋል።

የምርት ማሸጊያ ችግር ፣ ሳይበላሽ የሚቆይበት ፋሲሊቲ አለመኖር ፣ የገቢያ ትስስር አለመኖር በበላድርሻ አካላት መካከል የትስስርና ቅንጅት ደካማ መሆንን እንደ ችግር አንስተዋል።

በተጨማሪም በሎሚ ምርት ለመሰማራትና በሰፋፊ እርሻ ተሰማርቶ ለመስራት የሚፈልጉ ባለሃብቶች የባንክ ብድር አቅርቦት እንደማያገኙ ጠቅሰዋል። ሌላው በዚህ የውይይት መድረክ ላይ የቀረበው የነጭ ሽንኩርት እሴት ሰንሰለት የተመለከተ ሲሆን ነጭ ሽንኩርት ምርትና ምርታማነቱ እያደገ በመሄድ ላይ መሆኑን አቶ አማረ ጠቁመዋል።

ይህ እየጨመረ በመሄድ ላይ ያለው የነጭ ሽንኩርት ምርት እድገት ከተሰራበት ወደ ውጭ ተልኮ የሚገኘውን ምርት ማሳደግ ይቻላል ብለዋል ። እንደ ጂቡቲ ፣ ጊኒ ፣ ኬኒያ ፣ ናይጄሪያ ፣ ሱማሊያ ፣ ዩናይትድ ኪንግደም ፣ የመን ፣ ዩናይትድ ስቴትስ እና የተባበሩት አረብ ኢሜሬቶች መዳረሻ ቢሆኑም ፤ ሁሉም ሀገራት የሚላከው ምርት ተደምሮ ወደ ሱዳን ከሚላከው አይበልጥም ብለዋል። ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ገቢያ መር አሰራር መከተል የትና ለማን ነው የምንሸጠው የሚለውን በመለየት የገቢያ ትስስርን መፍጠር ይገባል ብለዋል።

እንደ ሎሚ ሁሉ በነጭ ሽንኩርት ዘርፍ ለሚሰማሩ አምራቾች ያለው የብድር አቅርቦት ውስንነት እንዳላበት ጠቁመዋል።

ሌላው በነጭ ሽንኩርት ላይ የሚታየው ችግር አርሶ አደሩ በባህላዊ መንገድ የሚያመርት በመሆኑና ምርታማነቱን ማሳደግ ላይ በራሱ የሚሰራው ስራ አለመሆኑም የራሱ አሉታዊ አስተዋፆ አለው ብለዋል።

በመሆኑም በሎሚም ሆነ በነጭ ሽንኩርት ላይ የሚስተዋል ችግሮችን ለመቅረፍ ሰፋፊ እርሻዎችን ማስፋፋት ፣ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለአርሶ አደሩ ማቅረብና የወጪ ንግድ መዳረሻ አገራትን ማብዛት ያስፈልጋል ብለዋል። በክላስተር የተመሰረተ አመራረትን መከተል ፣ ምርቱ ሳይበላሽ እንዲቆይ የሚደረግበትን ዘዴ መፍጠር ፣ የገቢያ ትስስር መፍጠር ስራ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

በተጨማሪም የጥራት ስታንዳርድ እንዲሁም እንደ ሌሎች ምርቶች ስትራቴጂ ሊቀርፅላቸው እንደሚገባ ምክረ ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል።

# በኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ ሥራ ላይ ባለሃብቶች እንዲሳተፉ መንግሥት ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ተጠየቀ



**በይድነቃቸው አለማየሁ**

መንግሥት በሚወስደው የአካካባቢ ጥበቃ እና አንክብካቤ እርምጃዎች በርካታ የቆዳ ፋብሪካዎች ከስረው እየተዘጉ እንደሆነ አንድ ጥናት አመለከተ። በኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ በተለይም በጨርቃጨርቅ እና የቆዳ ንዑስ ዘርፍ ላይ ስለሚሰተዋሉ የፖሊሲ እና የአሰራር ተግዳሮቶች ላይ ያተኮረውና አዲስ ቻምበር ያስጠናው ይኸው ጥናት እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ጋና ፣ናይጀሪ፣ግብጽ፣ቱኒዚያን እና ታንዛኒያ የመሳሰሉ አገራት የደረቅ እና ፈሳሽ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ማጣራት እና መልሶ ጥቅም በማዋል ቢዝነስ ዘርፍ ላይ የግሉን ዘርፍ በስፋት በማሳተፍ በአረንጓዴ ሽግግር ላይ ተጨባጭ ለውጥ አምጥተዋል ሲሉ ጥናት አቅራቢው አቶ እሰይ ታከለ ተናግረዋል።

የጨርቃጨርቅም ይሁን የቆዳ አምራቾች ለግብአት የሚጠቀሙዋቸው ከውጪ ከሚገቡ መርዛማ ኬሚካሎች ምትክ አገር በቀል እና ኦርጋኒክ የሆኑ ኬሚካሎች ቢጠቀሙ በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ብክለት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ እንደሚቻል የጥናቱ ምክረ ሃሳብ ይጠቁማል። የጨርቃጨርቅ እና የቆዳ ማልፊያ ፋብሪካዎች አብዛኛውን ጊዜ በከተሞች ዳርቻ ላይ የሚገነቡ በመሆኑ በአቅራቢያቸው የሚገኙትን ወንዞችን እና ዕጽዋት ይበክላሉ። በፋብሪካዎች በኩል የሚስተዋለው አንኳር ችግር ፋብሪካዎች የቆሻሻ ማከሚያ መሰረተ ልማቶቻቸውን በሥራ ላይ የሚያውሉት ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ጉብኝት በሚያደርጉ ሰሞን ሲሆን በሌላ ጊዜ ቆሻሻ ወደ አቅራቢያቸው ወንዞች መልቀቃቸው ነው ተብሏል። በኢትዮጵያ ከቆዳ ኢንዱስትሪዎች በቀን ወደ 150ቶን ፍሳሽ ቆሻሻ ይወገዳል። ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪዎችም እንዲሁ 1 ኪ.ግ ጨርቅ ለማምረት እስከ 83 ሊትር ኬሚካል መጠቀም ይጠይቃል፤በአመት እሰከ 33 ሜትር ኪዩብ ቆሻሻ ፍሳሽ ያመነጫሉ። ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ የፋብሪካ ማርዛማ ኬሚካሎችን ወደ ንጹሕ ውሕድ መቀየር አልያም መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ሥራ በአገር ደረጃ 5 በመቶ ብቻ ነው። ይህም ቁጥር በአፍሪቃ ከሚገኙ አገራት ጋር ሲወዳደር በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ጥናት አቅራቢው አስረድተዋል። አካባቢያችን ሳንጎዳ እና ኢንዱስትሪዎቻችንን ለማሳደግ ቢያንስ በእያንዳንዱ ወረዳ አነስተኛ ቄራዎችን መገንባት፤ በእያንዳንዱ ወረዳ የፍሳሽ ማጣሪያ እና ማከሚያ ማዕከላትን መገንባት ያስፈልጋል የሚሉት ምክረሃሳቦች በጥናቱ ተሰንዝረዋል። በውይይቱ ላይ በርካታ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ከተሳታፊዎች የተነሱ ሲሆን በአቅራቢዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥቷል። ይኸው ረቂቅ ጥናት በግብዓቶች ዳብሮ ለመግሥት የፖሊሲ ማሻሻያ ሰነድ ግብዓት ሆኖ እንደሚያገለግል ተነግሯል።

# መንግሥታዊ የውጭ ዕዳ በግል ዘርፉ ላይ ያለው ተጽእኖ




**በእጹብድንቅ ስለሺ (ዶ/ር)**

መንግሥታዊ የዉጭ ዕዳ( ካሁን በኋላ ‘ የዉጭ ዕዳ’ ተብሎ የሚገለጸው) ምንድን ነው? የውጭ ዕዳ የምንለው እንደ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ጃፓን ከመሳሰሉ ከበርቴ ሀገራት ወይም እንደ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም /IMF፣ የአለም ባንክ፣ የግል ንግድ ባንኮች ወይም የፓሪስ ክለብ ከመሳሰሉ ድርጅቶች የሚመነጨውን የአንድ ሀገር ብድር ነው(ሁሉም ዕዳ የዉጭ አይደለም:: አገሮች ካገር ዉስጥ በተለያየ መንገድ ሊበደሩ ይችላሉ:: መንግሥት የግምጃ ቤት ሰነድ ሲሸጥ እየተበደረ ነው:: የሚገዙት ትላልቅ ድርጅቶች፣ የግል ባንኮች ፤ሀብታም ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ:: ያሁኑ ትዉልድ ከሚመጣው ትዉልድ ሊበደርም ይችላል:: ግን ሳይከፍለው ቢቀርስ):: ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ትልልቅ የግል ኩባንያዎች ለሌሎች አገሮች መንግሥታት ብድር ሊሰጡ ይችላሉ:: እነዚህ ብድሮች ብዙውን ጊዜ የሚተመኑት እና የሚሰጡት ከተበዳሪው ሀገር የተለየ ምንዛሪ በመጠቀም ነው ( ለምሳሌ ኢትዮጵያ ስትበደር በብር ፋንታ ዩሮ፣ ፓዉንድ ስተርሊንግ፣ የን በመሳሰሉ ገንዘቦች ነው):: ይህም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ አገሮች የውጭ ምንዛሪ ገበያን እና የውጭ ብድርን ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖራቸው ያደርጋል::

የብድር እጥረት የምንዛሪ ጭማሪን ያስከትላል (ብር ዋጋዉ ይወርዳል፤ዶላር ይወደዳል):: የዉጭ ምንዛሪ ገበያዉ ደግሞ ለንግዱ ማህበረሰብም ሆነ ለአጠቃላይ ምጣኔሀብት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑና በአይነ ቁራኛ ከምንከታተላቸው ገበያዎች መሐከል ነው:: ከዚህ የተነሳ የዉጭ እዳን መጠን ማወቅ፣ አቅጣቻኡን መገምገምና በተለይ በግሉ የምጣኔሀብት ዘርፍ ላይ የሚኖረዉን በረከትም ሆነ የሚያስከትለዉን ጦስ በየጊዜው መመርመር እና የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ለዚህ ደግሞ የዉጭ እዳ መቼ እና በምን መንገድ የግሉን ዘርፍ ሊነካካ እንደሚችል ማሳየት ከመገናኛ ብዙሃን እና የምጣኔሀብት ባልሙያዎች የሚጠበቅ ተግባር ነው::

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የውጭ ብድር ከ27 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደሚሆን የተለያዩ አሃዛዊ የመረጃ ምንጮች ያሳያሉ:: ይህም የአጠቃላይ አገራዊ ምርት(GDP) ግማሽ የሚያህል የዉጭ ዕዳ አለብን ማለት ነው:: ወለዱን እና የዋናዉን አመታዊ ክፍያ ለማከናወን ባጠቃላይ ምጣኔሀብቱ ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ጫና መገመት ይቻላል( ከበርቴ አገሮች ራሳቸው ብዙ ብድሮች አለባቸው:: ልዩነቱ የነሱ ብድር አንድም ካገር ዉስጥ ነው:: ሁለትም በራሳቸው ገንዘብ ነው:: የሚፈጥረዉ ጫናም ልክ በማደግ ላይ ያሉ አገራት ሊገጥማቸው ከሚችለው በታች ነው::

በቅርብ ጊዜ፣ ከአለምአቀፉ የገንዘብ ተቋም ጋር የተወሰነው የብድር ክፍል ለማስከለስ እና እንዲሁም ተጨማሪ አዳዲስ ብድር ለማግኘት የሚያስችሉ ዉይይቶች በከፍተኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑካን እና የገንዘብ ድርጅቱ ወኪሎች መካከል ንግግሮች መካሄዳቸዉን ሰምተናል:: ፍሬ ማፍራታቸዉን ወይም እንዳይሳካ ያደረጉትን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሁም የቅድመ ሁኔታዎችን ምንነትና አገራዊ አንድምታ በግልጽ የነገረን የለም:: የዉጭ ዕዳን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ እና እንዲሁም አዲስ የብድር ዝግጅት ጥያቄ ሲኖር ከገንዘብ ድርጅቱ ብቻ ሳይሆን ብድር በሚራዘምበት ጊዜ የIMFን ግምገማ እና ምክር ከሚያስፈልጋቸው ሶስተኛ ወገኖች ጋር ውይይት እና ይሁንታ አስፈላጊ ነው:: የኢትዮጵያ የዉጭ ዕዳ በምን ምንዛሪ ነው? ዋና ዋና አበዳሪዎችስ እነማን ናቸው? ወደ ብድር ገንዘብ ስብጥር ስንመጣ አብዛኛው የኢትዮጵያ መንግሥታዊ የዉጭ ዕዳ በUSD ሁኖ ይገኛል:: SDR / special drawing rights( የአሜሪካ ዶላር፣ ፓውንድ ስተርሊንግ፣ የን.... ጨምሮ የምንዛሬ ቅይጥ ነው::) ዋና አበዳሪዎች እነማን ናቸው የተባለ እንደሆን የዓለም አቀፍ ልማት ማህበር/IDA (የዓለም ባንክ ወገን ነው)፣ አለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም፣ ማህበረ ፓሪስ/ the Paris Club፣ የቻይና የወጪና የገቢ ንግድ ባንክ(EXIM Bank of China) እና ሌሎች የግል ኩባንያዎች ናቸው::

ለመሆኑ አገሮች ለምን ይበደራሉ? ሀገራት የውጭ ብድር ዕዳ ዉስጥ የሚዘፈቁት የዉጭ ንግድ ሚዛናቸው በተዛባ ጊዜ ሚዛናቸውን ለማስተካከል ወይም አንዳንድ ጊዜ የበጀት ጉድለታቸውን ለመሸፈን ነው (የአገር ውስጥ ሃብትን ብቻ በመጠቀም መከናወን የማይችሉ የመሠረተ ልማት ውጥኖች ሲኖሩ ወደ አበዳሪ እጅን መዘርጋት ይመጣል):: ወደ ውጭ ከሚላኩ ሸቀጦችና አገልግሎቶች እንዲሁም ከውጭ ከሚመጣ ሙዋለ ንዋይ ፍሰት የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እና ከሌላዉ አለም ለምንገዛቸው ሸቀጦችና አገልግሎቶች ከሚያስፈልገው የምንዛሪ መጠን ያነሰ ሲሆን አገሮች የክፍያ ሚዛን ጉድለት ያጋጥማቸዋል:: ይህ በሦስት መንገዶች እንዲሟላ ማድረግ ይቻላል:: በውጭ ብድር ወይም በተወሰነ ደረጃ የውጭ እርዳታ ከተገኘ እንዲሁም ከምንዛሪ ጎተራ ያለዉን የገንዘብ ምርግ/ forex reserve በማሟጠጥ ሊሆን ይችላል::

የውጭ ብድር ከግሉ ዘርፍ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ይዟቸው የሚመጣቸው ገፀ በረከቶች ወይም ሊያስከትላቸው የሚችል ጦሶች ምን ምን ናቸው? የውጭ ዕዳ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ የሚያሳድረውን በጎም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ቢያንስ ከሶስት አቅጣጫዎች ማለትም የኢኮኖሚ እድገት፣ የገንዘብ ገበያ መረጋጋት( በተለይ የምንዛሪ ገበያው) እና የሀገር ውስጥ ማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን በመጠቀም ለመረዳት ይቻላል:: በደንብ ታስቦበት እና ከልክ ሳያልፍ የሚገኝ የዉጭ መንግሥታዊ ብድር የምጣኔሀብት እድገትን እንደሚያበረታታ የሚያሳዩ ጥናቶች እና ግምገማዎች አሉ:: የምጣኔሀብት ዕድገት ሲባል በአንድ አገር ዉስጥ በተውሰነ ጊዜ የሚሠራው ምርትና አገልግሎት መጠን መስፋፋት ማለት ነው( በዋናነት በመጠን):: በምጣኔሀብት ዕድገት ምክንያት አጠቃላይ የገበያ ፍላጎት መጨመር የግል ቢዘርፉን ተጠቃሚ ማድረጉ የማይቀር ነው:: እድገት በሚኖርበት ጊዜ የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች የሚያከናዉኗቸው ፕሮዠዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ ስለሚመጡ የንግድ ድርጅቶች ለሌሎች ንግዶች ወይም የመንግሥት አካላት የግብአት አቅራቢዎች ሆነው የማገልገል ዕድል ያገኛሉ:: ከዚህም በላይ እነሱ ራሳቸው በተሻለ የመደራደር ኃይል፣ በቂ መጠን እና ተፈላጊ ጥራት ያላቸውን ግብአቶች ለመግዛት ብዙ አማራጮች ሊኖራቸው ይችላል:: በጥቅሉ ገበያ ይስፋፋል፤ ንግድ ያብባል፤ ምጣኔሀብት ያድጋል:: ከልክ ያላለፉና በሥነ ስርአት ሥራ ላይ የዋለ የዉጭ ብድር ሲኖር( ትክክለኛ የዉጭ ብድር መጠን ስንት ነው? ለመሆኑ እንዲሁ በጥሬው ነው የሚለካው ወይስ ካለ አጠቃላይ ምጣኔሀብታዊ አቅም አንጻር? ብድር ምን ምን ሥራ ላይ ቢዉል ነው አገር የሚያሳድገው የግል ዘርፉንስ የሚያነቃቃው? እነዚህና መሰል ጥያቄዎችን በሌላ ክፍል አስነብባችኋለሁ)::

የውጭ ዕዳ ብዙውን ጊዜ በሰፊው ተቀባይነት ባላቸው የውጭ ምንዛሬዎች መልክ የሚሰጥ ነው:: ከዚህ የተነሳ ከውጭ አገር ሸቀጣ ሸቀጥም ሆነ የማምረቻ እቃ በማስመጣት የተሰማሩ ድርጅቶች የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ በማድረግ የውጭ ምንዛሪ መጠየቂያ ማመልከቻ ጊዜን በመቀነስ እና በአንፃራዊነት ከፍተኛ የሆነ የዉጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ ያስችላል:: የግሉ ዘርፍ ወሳኝ የሆኑ ግብአቶችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲያስገባ በማድረግ ምርቱን በማምረት ወደ ውጭ ለመላክ አልፎ ተርፎም ለራሳቸው እና ለአገሪቱ የዉጭ ገንዘብ forex እንዲያመነጩ ይረዳቸዋል:: በመሆኑም የውጭ ብድርና የግሉ ዘርፍ ሁለተኛው መጋመጃ መስመር የውጭ ምንዛሪ ገበያን በማረጋጋት እና ዋና ዋና የምርት ነክ ግብአቶችን ከውጭ ለማስገባት የሚያስፈልጋቸውን የውጭ ምንዛሪ በወቅቱና በአግባቡ ለማግኘት ማስቻሉ ነው በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የዉጭ ምንዛሪ እጥረት ያልተፈታ ችግር ሁኖ በሚገኝባቸው አገሮች::

ሌላው የውጭ ብድር እና የንግዱ ማህበረሰብ ትስስር መስመር እንደ ግብር፣ የመንግስት ወጪ፣ የሀገር ውስጥ ብድር እና የወለድ ተመንን በመሳሰሉት የማክሮ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# አዲስ ቻምበር ለሲኒየር ባለሙያዎችና የማኔጅመንት አባላት የአመራር ክህሎትን ማሳደግ የሚያስችል ስልጠና ሰጠ



**በከፍያለው ዋሲሁን**

‹‹Growth mind set for leadership effectiveness›› በሚል ርዕስ ለምክር ቤቱ ሰራተኞች ክህሎቶቻቸውን ማዳበር በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ነው ስልጠናው የተሰጠው::

የአዲስ ቻምበር ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም ንግድ ምክር ቤት 77 ዓመት ማስቆጠሩን አስታውሰው ፤ ንግድ ምክር ቤቱ ለአባላቱ ለሚሰጠው አገልግሎት መቀላጠፍ ለውጥ እና እድገት ያስፈልጋል ብለዋል:: እንዲህ አይነት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች የምክር ቤቱን ስትራቴጂክ እቅድ እንዲሳኩ በማድረግ እና የሚጋጥሙ ችግሮችን በቀላሉ ለማለፍ አይነተኛ ሚና እንደሚጫወት ዋና ጸሀፊው አክለው ገልጸዋል::

የ SAK ቢዝነስ እና ፐርሰናል ዲቨሎፕመንት መስራችና ስራ አስኪያጅ አደራ አብደላ (ፒ.ኤች.ዲ) በሰጡት ስልጠና በተሰማራንበት ስራ ውጤታማ ለመሆን የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ይገባል ብለዋል:: እንደ ባህል ፤ እምነት ፤ ማህበረሰብ ፤ ትምህርት እና አካባቢ የልቡና ወቅር ( ማይንድ ሴት ) የሚቀርፁ መሆናቸውን ጠቅሰው ፤ይህንን መቀየር ያስፈልጋል ብለዋል:: በመሆኑም የንግድ ምክር ቤቱ ስራተኞች በስራቸው ስኬታማ እንዲሆኑ መማርና መሻሻል ላይ ትኩረት ማድረግ ፤ ጠንክሮ መስራት ፤ ዲስፐሊን እና መልካም ልማድን ለማሳደግ መስራት እንደሚገባ ገልፀዋል::

የድርጅቶች ውድቀትና መነሳት ካላቸው እቅድና ግብ በተጨማሪ ስራተኞች እራሳቸውን ለፈታኝ ስራዎች እጅ ሳይሰጡ ጠንክረው በመስራት የልቦና ውቅር በማሳደግ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ገልፀዋል::

በስልጠናው ላይ የተገኙ የምክር ቤቱ ስልጣኞች ባገኙት ስልጠና መደሰታቸውን ገልፀው አደራን (ፒ.ኤች.ዲ) አመሰግነዋል ::

# አምራች ዘርፉ የቴክኒክ እና ሞያ ተቋማትን በመደገፍ ረገድ ሚናው ከፍ ያለ መሆኑ ተገለጸ!



የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የ20ኛ አመት ምስረታ በዓሉን በባለፈው ህዳር ወር ውስጥ በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል::

የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የ20ኛ ዓመት የምስረታ በአሉን ማክበር በጀመረበት ወቅት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትር ዲኤታ አቶ ሃሰን መሃመድ እና ሌሎች ባለድርሻዎች እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት የአምራች ዘርፉ ስኬቶች ተግዳሮቶች እና የወደፊት አቅጣጫ ላይ ያተኮረ ውይይት ተካሂዶ ነበር:: በውይይቱ አምራች ዘርፉ በመንግስት ትኩረት የተሰጠው ቢሆንም ብቁ የሆነ የሰው ሃይል ባለመኖሩ ምክንያት ውጤታማ መሆን እንዳልቻለ በወቅቱ በነበረው የውይይት መድረክ ላይ ተጠቁሟል::

የቴክኒክ እና ሞያ ተቋማት ለኢንዱስትሪዎች ብቁ ባለሞያ ከማቅረብ አንጻር በሚገጥሙ ችግሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ለውይይት መነሻ ጽሁፍ ያቀረቡት ዶ/ር ገነነ አበበ አምራች ዘርፉን ከሚገዳደሩት ችግሮች መካከል ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው የበቁ ባለሞያዎች አለማግኘት እንደሆነ ጠቅሰዋል::

የቴክኒክ እና ሞያ ተቋማት ላይ ባለው የአመለካከት ችግር ምክንያት አምራቾች ከነዚህ ተቋማት የሚወጡ ባለሞያዎች ላይ እምነት ጥሎ ቀጥሮ ለማሰራት ችግር እየተፈጠረ መሆኑንም አንስተዋል::

ተቋማቱ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እና የማሽነሪ ግብአት የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ተከትሎ ከሌሎች የትምህርት ተቋማት ባነሰ በጀት የሚያዝላቸው መሆኑ በራሱ ተማሪዎች ብቁ ባለሞያ እንዳይሆኑ እያደረጋቸው መሆኑን አንስተዋል::

አምራች ዘርፉ የሚፈልገውን ባለሞያ ለማግኘት ከቴክኒክ እና ሞያ ተቋማት ጋር ያለውን የቅንጅት ስራ ማጠናከር እንደሚያስፈልግ እና በገንዘብም ሆነ በሞያ ስልጠና መደገፍ ወሳኝ መሆኑን በምክረ ሃሳባቸው አቅርበዋል::

በውይይቱ ላይ የአምራች ዘርፉ ስኬቶችን እና ተግዳሮቶችን እንዲሁም የፋይናንስ ተደራሽነትን እና ዲጂታል ፋይናንስን የተመለከቱ ለውይይት መነሻ የሆኑ ጽሁፎች የቀረቡበት መድረክ ነበር::

# በአምራች ዘርፍ ለተሰማሩ ሴቶች የንግድ አመራር ክህሎት ስልጠና ተሰጠ



**በሰናይት እሸቱ**

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በአምራች ዘርፉ ለተሰማሩ ሴቶች በተሰማሩበት ዘርፍ የሚገጥሟቸውን የአመራር ክህሎት ክፍተቶች በመለየት የአመራር አቅማቸውን ለማሳደግ የሚያግዝ ስልጠና ሰጥቷል::

በስልጠናው በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት፣ በምግብ፣በቆዳ፣በቡና ማቀነባበር እና ሌሎችም የተሰማሩ አምራቾች ተሳትፈዋል::

በስልጠናው ተሳታፊዎች በተሰማሩበት የስራ መስክ ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ስራቸውን እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማህበራዊ ግንኙነቶቻቸውን አቻችለው በመሄድ የሚፈልጉበት ውጤት ላይ መድረስ እንደሚችሉ ልምዶቻቸውን አጋርተዋል::

ሴቶች አመራርነትን ወደንግዱ ሳይገቡም በቤት ውስጥ የሚያቁት እና የሚተገብሩት ቢሆንም፡ ወደንግዱ ለገቡት አጋዥ ስልጠናዎች የሚያቁትን የበለጠ ወደ ውጤት እንዲቀይሩ እንደሚያደርጋቸው ተገልጿል::

ስልጠናውን የሰጡት በግል በማማከር ዘርፍ የተሰማሩት አቶ አሸናፊ አበራ እንዳሉትም ከአምራች ዘርፉ ጋር በተያያዘ ለውጤታማነቱ በርካታ ጉዳዮች የሚነሱበት ቢሆንም የአመራር አቅምም አንዱ በመሆኑ መሰል ስልጠናዎች በምክርቤቱ ቀጣይነት ሊኖራቸው የሚገባ እንደሆኑ ጠቁመዋል::

# መንግሥታዊ የውጭ ዕዳ በግል ዘርፉ ላይ ያለው ተጽእኖ

ከ ገጽ 5 የዞረ

ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በኩል ነው:: መንግሥታት የበጀት ጉድለታቸውን ከውጭ ምንጮች መሙላት በማይችሉበት ጊዜ፣ በዋናነት የግብር መጠንን እና አይነትን በመጨመር የግሉን ዘርፍ ሊያደናቅፍ ወደሚችል በጀታዊ/ፊስካል ፖሊሲ ሊያዘነብሉ ይችላሉ:: ይህም የግል ድርጅቶችን ወጪያቸውን በመጨመር፣የገበያ ዋጋ ከፍ እንዲያደርጉ በማድረግ የምርቶቻቸውን ፍላጎት በመቀነስ ንግድን ያቀዛቅዛል በዚህም ትርፋማነታቸው እንዲቀንስ ወይም እንዲከስሩ ሊያደርግ ይችላል:: ከዚህም በላይ እንደ የግምጃ ቤት ሰነዶች ሽያጭ ያሉ የገንዘብ ፖሊሲዎች በአገር ውስጥ የሚዘዋወረዉን የገንዘብ መጠን ይቀንሳሉ ይህም የንግድ ልዉዉጦች እንዲቀዛቀዙ ስለሚያደርግ (የሸቀጦች እና የአገልግሎቶች ፍላጎት ይቀንሳል) የአጠቃላይ ምጣኔሀብቱን እና የግል ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተጓጉላል:: በመጨረሻም የዉጭ ዕዳ ክፍያ ሲጀመር ከላይ ያየናቸውን የዉጭ ዕዳ ለንግዱ ማህበረሰብ የሚያመጣቸውን ጥቅሞች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመቀልበስ የንግድ ድርጅቶችን ሊጎዳ ይችላል:: ቀደም ሲል እንደተብራራው (የብር የመግዛት አቅም እየደከመ ይሄዳል):: ይህም የውጭ ምንዛሪ እጥረት መባባስ እና ከውጭ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ የዋጋ ንረትን ያስከትላል::

ከፍተኛ የውጭ ብድር በገበያው ላይ ፍትሃዊ ያልሆነ ውድድር የሚያስከትል እንዲሁም ሙስናንም ሊያስከትል ይችላል:: አንዳንድ ባለስልጣናት እና ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ያላቸው ጥቂት ሀብታሞች ከውጭ በብድር የሚገኘውን ገንዘብ ከተቆጣጠሩ ምጣኔሀብት ላያድግ ይችላል:: የውጭ ምንዛሪ ገበያዉ እንደታሰበዉ እንዲሁ አይረጋጋም:: ይህ በብዙ ታዳጊ ሀገራት በብድር የተገኘ ገንዘብ ስታለመለት የህዝብ ሥራ መዋሉ ቀርት በተለያዩ የዉጭ አገራት ባንኮች እንዲቀመጥ ሊደርገ ይችላል:: ይህ ደግሞ አገሪቱ ዕዳዋን መክፈል ወደማትችልበት ሁኔታ ሊያመራት ይችላል:: ከዚያም የተብዳሪነት አመኔታ እንዲቀንስ/ low credit rating በማድረግ ተጨማሪ ብድር በቀላሉ እንዳይገኝ በማድረግ፣ ቢገኝ እንኳን ወለዱ እጅግ ከፍተኛ ስለሚሆን ከብድር የሚገኘው ትሩፋት እንዲመናመን ያደርጋል::

ለማጠቃለል ያህል የውጭ ብድር በአግባቡ ከተያዘ የሀገርን መሠረተ ልማቶች መዘርጋት እና የሸቀጦችና አገልግሎቶችን በብዛትና ጥራት በማስፋፋት ምቹ የንግድ ሁኔታን ይፈጥራል:: የውጭ ብድርን በብልኀት በመጠቀም ሊመጣ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ እና በወቅቱ ማግኘት ማስቻሉ ሌላው የግል ዘርፉ ጥቅም ነው( የውጭ ምንዛሪ ገበያን በማረጋጋት):: የዉጭ ብድር መገኘት ፣ መንግሥት በግል ዘርፉ ላይ ግብር እና ከፍተኛ ወለድ የመሳሰሉ ጫናዎችን እንዳያሳድር ለጊዜዉም ቢሆን ይታደጋል:: ነገር ግን በኢኮኖሚው ውስጥ ሙስና እና ኢፍትሃዊ ፉክክር ካለ በውጪ በብድር የሚገኘው ገንዘብ በአጠቃላይ ሀገሪቱና በተለይም በንግዱ ማህበረሰብ ላይ ጠንቅ ስለሚሆን በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል::

# ንግድ ምክር ቤቱ ለሴት የቢዝነስ መሪዎች በሥነ ጾታ ሥርዓት አተገባበር ላይ ሥልጠና ሰጠ





**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በአገራችን ለሥርዓተ ጾታ የተሰጠው የፖሊሲ ትኩረት፤ሴቶች በስራ ፈጠራ እና በንግድ ሰራ አመራርነት ማሳተፍ ያለው ሚና እና ሴት ስራ ፈጣሪዎችን እና አመራሮችን ማሳደግ የሚቻልባቸው ስልቶች የሚሉት ነጥቦች የስልጠናው ዓላማዎች ናቸው::

የአገራችን ሕብረተሰብ ለሴቶች የሚሰጠው የተዛባ ግምት ረዥም ዘመናትን የስቆጠረ ነው:: ይህም ሴቶች ለብዙ ማሕበራዊ፤ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ባይተር ሆነው አንደቆዩ ተወስቷል:: ነገር ግን ከቅርብ አመታት ወዲህ በሕብረተሰቡ ዘንድ የቆየው አስተሳሰብ እየተቀየረ መጥቷል::የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማሳደግጥሩ ጥሩ ፖሊሰዎቸ፤ሕግጋት እና የሥርዓተ ጾታ መመረያዎች ቢኖሩም ገና ብዙ መሥራት አለብን ይላሉ ስልጠናውን የሰጡት አቶ መዝገቡ በላይ:: ጥናቶች አንደሚያሳዩት በቢዝነሱ ዓለም የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ እርምጃ ከሚገድቡት ዋና ዋና ተግዳሮቶች መካከል፡ የገንዘብ ድጋፍ ማጣት; ውስብስብ የአስተዳደር ሂደቶች፤ ንግድ ለመጀመር ኪሣራ ይከሰታል ብሎ መፍራት የሚሉት ይገኙበታል:: በተለይም ኪሳራን መፍራት አስመለክቶ በቅርቡ የአውሮፓ ኮሚሽን ያወጣው ጥናት መሠረት ኪሳራን መፍራት ሴቶች የራሳቸውን ሥራ(ቢዝነስ ) ለመፍጠር የሚያደርጉትን ጥረት ከሚገድቡ ትልልቅ እንቅፋቶች መካከል 43 በመቶ ድርሻ ይይዛል::

ሌላዋ አሰልጣኝ ወ/ሮ ወርቁ ሃይሉ በበኩላቸው በንግድ ሥራ (በቢዝነስ ኩባንያ አመራር እና ውሳኔ ሰጪ ለመሆኑ የበቁ ሴቶች ቁጥር ዛሬም አነስተኛ ነው:: ዛሬ ላይ በዓለም ከ500 ትላልቅ ኩባያዎች መካከል በሴቶች የሚመሩት በአማካይ ከ 50 አይበልጥም ብለዋል::

የፆታ እኩልነትን ለማጎልበትና ሴቶችን በኢኮኖሚና በአመራር ክህሎት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ በንግድ ስራ አመራር ቦታዎች ላይ ሴቶችን በበቂ ሁኔታ ማሳተፍ ፤ በሴቶች ባለቤትነት የሚመሩ ድርጅቶች ስራቸውን በተሻለ መንገድ ማከናወን የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን መንደፍ እና በተገቢ መንገድ መተግበር፤ሴቶች ለተለያዩ ኩባንያዎች የቦርድ አባልና ሃላፊ እንዲሆኑ ማገዝ፤ ተቋማት ለፆታ እኩልነት ተጠያቂ እንዲሆኑ ተቋማዊ ፖሊሲ እና አሰራሮች መዘርጋት የስፈልጋል የሚሉት ነጥቦች በጥናቱ ከተሰነዘሩ ምክረ ሃሳቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

# አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት

## ADDIS ABABA CHAMBER OF COMMERCE AND SECTORIAL ASSOCIATIONS

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ ለአባላቶቹ እና ለመላው የንግዱ ህብረተሰብ በዲጂታል የታገዘ የ2024-2025 እትም የቢዝነስ ዳይሬክተሪ/ የንግድ ማውጫ/ እነሆ እያዘጋጀ ይገኛል።

ይሄው በሞባይል እና በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መተግበሪያ ዘዴዎች የተዘጋጀው የንግድ ማውጫ ፣ ለነጋዴዎች፣ ለውጪ ባለሃብቶች፣ለስራ ፈጣሪዎች፣ለውጪ ሀገር ዲፕሎማቶችና ሚሲዮኖች ፈጣን የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

በየሁለት አመቱ ታትሞ በሚሰራጨው እትም ላይ የድርጅትዎን ምርትና አገልግሎት በሀገር ውስጥ እና በአለም ዙሪያ እንዲያስተዋውቁ አዲስ ቻምበር በአክብሮት ይጋብዛል።

የኩባንያዎትን የቢዝነስ መረጃ በንግድ ማውጫው ላይ በማስፈር በየትኛውም የአለም ገበያ ላይ ለሚሊዮኖች ተደራሽ ይሁኑ!!!

ይቻላል
It's Possible!

ንግድ ምክር ቤት ህንፃ ሚክሲኮ አደባባይ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Chamber of Commerce Building Mexico Sq. Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ/Tel: +251 115 518055 ፋክስ/Fax: +251 115 511479
P.O.Box 2458 አዲስ አበባ፣ ኢትዩጵያ/Addis Ababa Ethiopia ኢ. ሜይል/E-mail: Infor@addischamber.com



# የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

## ለአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኀበራት ምክር ቤት አባላት በሙሉ

አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኀበራት ምክር ቤት ታህሳስ 11 ቀን 2016 ዓ/ም በኢንተር ሌግዠሪ ሆቴል ከጠዋቱ 2:30 ጀምሮ 17ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ያካሂዳል።

ጉባኤው የ2015 በጀት ዓመት የሥራ ክንውንን ይገመግማል። የውጭ ኦዲተሮች የሚያቀርቡትን ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል። በመሆኑም በዚህ ለምክር ቤታችን የወደፊት እርምጃ እጅግ ወሳኝ በሆነ ጉባኤ ላይ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ቦታ ተገኝተው እንዲሳተፉ የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ቢሆን፣ ለዚሁ የተዘጋጀውን የውክልና ደብዳቤ የያዙ የድርጅትዎን ባልደረባ መላክ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

ይቻላል
It's Possible!

አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኀበራት ምክር ቤት
ለተጨማሪ መረጃ፣
በስልክ ቁጥር 011 5513814፣ 5519817፣5514517፣5528205፣ 5518055 የውስጥ መስመር 214/222/202 በመደወል የምክር ቤቱን ባልደረቦች ማነጋገር ይቻላል።

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# Addis Ababa Chamber of commerce and Sectoral associations Terms of reference to conduct "Business Leadership Training for Business Women Leading SMEs"

**I. Background**

Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectorial Associations (AACCSA) is a voluntary Business Membership Organization (BMOs) established by the General Notice Number 90/1947 as an autonomous, non-governmental, non-political, and non-profit making organization. It was re-registered as per proclamation number 341/2003 with a mission of promoting business and investment by providing demand driven services to the best satisfaction of its members and advocating for favorable business environment.

AACCSA places a special emphasis on building business communities' capacity and providing demand-driven business training to members of the local business community in order to assist them in acquiring the knowledge and skills required for success in today's challenging business environment.In line with this AACCSA has been running a project in partnership with Danish Confederation Industries which includes an intervention program to build the capacity of member business companies in general and women lead SME businesses in particular. Small and Medium Enterprises (SMEs) plays a vital role in most economies, particularly in developing countries. They account for the majority of businesses worldwide and are important contributors to job creation and global economic development. In Ethiopia the development of small and medium enterprises play a key role in Ethiopia's drive to reach middle-income country status. SMEs not only serve as important to creating job opportunities, but they also contribute to the country's economic growth, particularly as a catalyst for the shift to an industrialized society. However, there are barriers confronting the success of SMEs. While some of the constraints to SMEs growth relate to external factors over which the enterprise has less control, others relate to the leadership capacity and knowledge of SME leaders. Therefore, to address the latter constraints, working on their leadership skills development through capacity building and training is vital. Considering this, AACCSA in collaboration with Danish Confederation Industries (DI-SPAII project) plans to organize the training for its members drawn from Women Led SMEs.

**II. Objectives of the training**

The objective of the training is to enhance the capacities of women business leaders to transform themselves so that they can effectively realize their visions, to become more proactive in managing their careers, to examine their managerial skills in order to promote personal strengths at work, to examine their experience with other experience of women business leaders.

**III. Methodology**

The trainer will apply multiple techniques to properly deliver the required training and to achieve the objectives of the training. She/he is expected to use various types of methodologies like power point presentation, Group discussions, experience sharing, related demonstrations, etc.

**IV. Scope of the Assignment**

The training should cover;

- Leadership concepts and its various styles;
- Leadership in relation with Decision making, communication, negotiation, work-life balance, time management, and personal growth etc.
- Leadership Challenges with practical examples;
- Women business leadership challenges with practical examples;
- Barriers to development for women leadership;
- Way outs for the challenges/barriers with best practices;
- Opportunities of women business leaders; the unique value proposition of women in business leaders.
- Other issues that the trainer assumed to be pertinent to the area of the training;

**V. Deliverables**

The trainer is expected to deliver:

- Presentation at the training session which is estimated to be 8 hours/one full day/ for about 30 participants;
- Power point presentation slides and
- Training report within a week after the training.

**VI. Expected Results**

At the end of the training program, participants will be able to:

- Acquire the relevant leadership skill needed in different situations.
- Recognize relevance of leadership role in business management
- Question their past leadership experiences and explore new way of leadership styles
- Capture best practices in leadership
- Exchanged knowledge regarding the challenges and opportunities
- Learn and practice the skills necessary to succeed and reach goals in cooperation with the employees.
- Learn how best to match the leadership needs and demands of the employees in the organization in terms of relevant leadership and clear goals and decision making.
- Enable to address challenges facing women business leaders.
- Strengthen their leadership network
- Generally, the training is required to be impact full which the participants can be well-prepared to upgrade their business to the next level.

**VII. Duration and Venue**

The training shall be delivered for one full day (8 hours) in Addis Ababa at selected hotel.

**VIII. Selection Procedure**

Selection of candidates will be based on the financial and technical proposals.

Evaluation Criteria and Weight

- Financial evaluation – 20 %
- Technical evaluation –80%

**IX. Required qualification and experience**

The trainer is required to meet the following requirements:

- MSc/MA degree in Social science and other related fields; (25%)
- Minimum of five years' experience in conducting trainings in leadership; (50%) and.
- Experience in entrepreneurship or business development training (25%).

**X. Applications**

Interested applicants can collect the detailed ToR from Mexico Square, Chamber Building; Applicants can submit technical and financial proposals with a separate sealed A-4 Size Envelope to Procurement and Property Administration Department Chamber's building, 1st floor, office number 12. The proposal, to be submitted should be in English and shall include the following:

**A. Technical proposal**

- it incorporates understanding of the assignment, proposed methodology and approaches, short description of deliverables and candidate's qualification, demonstrated experience and exposure to the assignment.

**B. Financial Proposal indicating :**

- All costs to conduct this assignment (including VAT) in ETB.

**Contact address**
Membership Development and Support Department
Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations
**Tel:** 0115519817/ 0115514517/0115518055/226 **Email:** Membership.addischamber@gmail.com

# Addis Chamber Training Institute (ACTI)

## List of Upcoming Training Programs

| No. | Training Topic | Date | Time | Training Fee | | Venue | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | Member | Non-Member. | | |
| 1 | Training of Trainers | November 28-30, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 2 | Effective Report Writing & Presentation Skills | December 4-8, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 3 | Procurement Management | December 4-8, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 4 | Secretarial Science and Office Operations Management | December 5-6, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 5 | Human Resource Management | December 5-7, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 6 | International Financial Reporting Standards | December 11-29, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 8,625 | 10,350 | ACTI | 15 half days |
| 7 | International Trade Service & Ethiopian Export/Import Practice | December 11-15, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 8 | Secretarial Science & Office Operations Management | December 12-13, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 9 | Supervisory Management | December 12-14, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 10 | Customer Relationship Management | December 18-22, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 11 | Business Communication | December 19-20, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 5,929 | 7,115 | Hotel | 2 full days |
| 12 | Transformational Leadership | December 19-20, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 13 | Rules and Regulations of VAT & Income Tax | December 25-29, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 14 | Strategic Decision Making and Problem Solving | December 26-28, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |

**For further information, please contact the Training Institute through 011-551-3882, 011-551-8055 ext. 229, 0911194965, 0911343078, dejedesalegn@gmail.com and hiwottlhn9@gmail.com**